# *በአማራ ክልል ከተሞች እየተስተዋሉ ለሚገኙ የጸጥታ ስጋቶች ተጠያቂው አዴፓ ነው!*

*(እያሱ ወልደ-ነጎድጓድ)*

*ሠላም ለማነኛውም የልማት እንቅስቃሴ የጀርባ አጥነት ነው፤ ያለ ሰላም ልማት ይቅርና ከቤት በሰላም ወጥቶ በሰላም መመለስ አይቻልም። ለአንድ ከተማ የሰላም መከበር መንግስትና ህዝቡ በጋራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል ነገር ግን መንግስት ዋናውን ሚና ሊጫወት ይገባል።*

*በአሁኑ ወቅት የከተሞቻችንን ጸጥታ ለማስከበር ሦስት አካላት ወሳኝ ሁነው ይታያሉ እነረሱም የክልሉ ወጣቶች፣ መንግስትና ቀሪው የከተማ ነዋሪ ናቸው።*

*በአማራ ክልል ከተሞች የሚገኙ ወጣቶች የከተሞቻቸውን ሠላም ለማስከበር ከፍተኛ አስተዋፆ ሲያደርጉ ቆይተው ነበር። ነገር ግን በአሁኑ ሰአት ሞራል አልባው አዴፓ የወጣቶችን ማህበር በማጠናከርና የከተሞችን ሰላም ማረጋገጥ ሲገባው ወጣቶችን በአሉታዊ ጉን በመመልከት ማህበራቱን እውቅና በመንሳትና ወጣቶችንም በማሰር ላይ ይገኛል። ስለሆነም አዴፓ የከተሞችን ጸጥታ በማስፈንና ለማትን በማፋጠን ትልቅ ሚና የነበራቸውን ወጣቶች እንዲገለሉ እያደረገ ይገኛል።*

*በሌላ በኩል የአማራ ክልል መንግስት ፖሊሶች የከተሞችን ጸጥታ ማስከበር ሲገባቸው ህዝብ በጠራራ ጸሃይ ንብረቱን ሲዘረፉና ሲደበደብ ምንም አይነት እርምጃ ሲወስዱ አይታዩም፤ ምክንያቱም የመንግስት ድጋፍ የላቸውም። ፖሊሶች የክልሉ መንግስት ከለላ ስለማይሰጣቸው በህገ -ወጦች ላይ እርምጃ ለመውሰድ ወኔ አይታየባቸውም። ስለሆነም ዛሬ በውቢቷ የክልሉ ርእሰ ከተማ ባህር ዳርን ጨምሮ በሌሎች የክልሉ ከተሞች ከፍተኛ የሆነ የቀን ዝርፊያ በእጅጉ ተስፋፍቷል፤ ልጅን በሰላም ሸኝቶ ሰዶ በሰላም መመለሱን እርግጠኛ የሚሆን ቤተሰብ የለም ፤ በከተሞች የሚገኙ ወላጆች ሁሉ ቀኑን የሚያሳልፉት በስጋት ነው።*

*የክልሉ መንግስት፤ ፖሊስና የወጣቶች አለመናበብ የከተማውን ህዝብ ሽብር ውስጥ ከቶታል። የከተማው ነዋሪ ሌቦችን ቢጠቁም፣ እጅ ከፈንጅ ይዞ ለፖሊዝ ቢያስረክብ ፖሊስ በበነጋተው ይለቀዋል፤ ይባስ ብሎ የተለቀቀው ሌባ በጠቋሚው ግለ ሰቦች ላይ ዛቻና ማስፈራራት እየጨመረ በመምጣቱ የከተማ ነዋሪዎች ሌቦችን ከማጋለጥ እየተቆጠቡ መጥተዋል። በዚህም ህገ -ወጦች በክልሉ ከተሞች ያለምንም ከልካይ አንደ አሸን እየበዙ በተቃራኒው የከተሞች ፀጥታ እንኳንስ ለእንግዳ ለነዋሪው አስፈሪ እየሆኑ መጥተዋል።*

*በጥቅሉ የአማራ ክልል መንግስት ለክልሉ ሠላም መስፈን ከፍተኛ አስተዋፆ ያላቸውን ወጣቶች፤ ፖሊሶችና የከተማውን ነዋሪዎች ተስፋ በማስቆረጥ የክልሉ ከተሞች ጸጥታ አሳሳቢ ደረጃ እንዲደርስ በማድረገ ከልሉ የልማት ሳይሆን የስጋት ቀጠና እንዲሆን እያደረገ ይገኛል።*